Coptic Orthodox Patriarchate
His Holiness Pope Tawadros II
Pope of Alexandria and
Patriarch of the See of St. Mark
The Papal Center

بطريركية الأقباط الأرثوذكس
قداسة البابا الأنبا تواضروس الثاني
بابا الأسكندرية
وبطريرك الكرازة المرقسية
المقر البابوي

Ⲧⲁⲱⲁⲇⲣⲟⲥ

222 Ramses St., Abbaseya, Cairo, Egypt — 222 شارع رمسيس ، العباسية ، القاهرة ، مصر
Tel: 024822580 Fax: 0235365880 email: office@popetawadros.org 0235365880 :فاكس 024822580 :تليفون


*Amharic – Nativity 2025*

**በስመ አብ፣ ወወልድ፣ ወመንፈስ ቅዱስ፣ አሐዱ አምላክ፣ አሜን።**

መልካም አዲስ አመትና መልካም የልደት በዓል ይሁንላችሁ፡፡ የተወደዳችሁ በኮፕቲክ ቤተክርስቲያን ያላችሁ ሁሉ፣ እንኳን አደረሳችሁ።እንኳን ለአዲሱ ዓመት ለ2025 ዓ/ም አደረሳችሁ።እና በጎርጎርዮሳዊያን ዓመት ካሉ ታላላቅ በዓላት የመጀመርያ ለሆነው ለታላቁ የልደት በዓልም፡፡ሁሉም አባቶች፣ ሜትሮፖሊታኖችና ጳጳሳት እንኳን አደረሳችሁ፡፡አባቶች፣ ሄጉመኖች፣ ቀሳዉስትና ዲያቆናት ሁሉ እንኳን አደረሳችሁ፡፡የቤተክርስቲያን ሰበካ ጉባኤያትና ሁሉም የኮፕቲክ ቤተሰቦች እንኳን አደረሳችሁ፡፡በመላው ዓለም ያላችሁ አዳጊዎችና ሕጻናት ክርስቶስን እንደ ትንሽ ሕጻን በምንቀበልበት በታላቁ የልደት በዓልእንኳን አደረሳችሁ፡፡ እግዚአብሔር ወደ ዓለም መግባትን በወደደ ጊዜ የልጅነትን መንገድ መረጠ።በዚህ ትንሽ ሕጻን ታላላቅ ስራዎች ተፈጽመዋል፡፡በእርግጥም የልደቱን ክስተቶች ስናጠና በጣም አስፈላጊ የሆነ እውነታ እናገኛለን፡፡ትንንሽ ነገሮች ሁሉ በእግዚአብሔር እጅ ሲቀመጡ ታላቅ ይሆናሉ። ለዚህ ምሳሌዎችን እሰጣለሁ፡፡

በልደት ታሪክ ውስጥ ትንሿን የቤተልሔምን መንደር አገኝተናል፣የተሸሸገች እና የማትታወቅ መንደር፡፡ በብዙ የዓለም ክፍሎች በሺዎች የሚቆጠሩ መንደሮች አሉ። ይቺ መንደር ግን ቅድስት ድንግል ማርያምንና ጠራቢው ቅዱስ ዮሴፍን ስትቀበል እና የጌታ የክርስቶስ ልደት ቦታ ስትሆን መንደሯ በዓለም ካሉት መንደሮች ታዋቂዋ መንደር ሆነች፡፡ይህች መንደር የቤተልሔም መንደር ነበረች።ትንሽ ነገር በእግዚአብሔር እጅ ሲሆን እጅግ ታላቅ ይሆናል።

መንደሯ ብቻ ሳትሆን ወጣቷ ልጅም ነበረች።የኛ እናት፣ ድንግል ማርያም።ዕድሜዋ ለጋ የሆነ ወጣት ልጅ ነበረች።እግዚአብሔር ግን ጸጋን ሞላባት።መልአኩም እንዲህ አላት፣መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፣ስለዚህም ደግሞ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል (ሉቃስ 1፡35)። ይህች በጣም ወጣት እና ትሑት ሴት ልጅ ፣ በመቅደስ የኖረችበኋላ በክርስትና ሕይወት ውስጥ በጣም ታዋቂዋ ቅድስት ሆነች።አሁን "የሰው ዘር መመኪያ" እንላታለን።የመላው የሰው ዘር፣ በሁሉም ቦታ ያሉ የወንዶች እና የሴቶች መመኪያ። እንዳልኩት አንዲት ትንሽ ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር ስትነጋገር፣እና በጸጋ ስትሞላ፣ እንደዚህ ድንቅ ትሆናለች።

ሦስተኛ ምሳሌ ኮከቡ ነው (ማቴዎስ 2፡2)።አንድ ትንሽ ኮከብ በሰማይ ላይ ታየ፤ምናልባት ባልተለመደ ሁኔታ ይንቀሳቀስ ነበር። እንደ ስነ ፈለክ ጥናት ከተመለከትነው።ከምስራቅ የሚመጡ ሰብአ ሰገልን መራቸው።እነዚህ ሰብአ ሰገል በጉዟቸው ይህ ኮከብ እንደ ብቸኛ መሪያቸው ነበር።ሲንቀሳቀሱ ይህ ኮከብ ተንቀሳቅሷል፣ሲቆሙም ቆመ።ተአምር ሆነ።ሰማዩ ስፍር ቁጥር በሌላቸው ዋክብት የተሞላ ነው።ነገር ግን ይህ ኮከብ፣ የልደቱ ኮከብ፣ ተአምር ሆነ፣ ታዋቂ ሆነ። የልደት ስዕሎችን ስናሳይ፣ ይህንን ኮከብ በሁሉም አይነት ስዕሎች መሳል አለብን።

ብዙ ምሳሌዎች አሉ፤ ትንሽ ነገር በክርስቶስ እጅ ታላቅ ይሆናል።ጥቂቱ በክርስቶስ እጅ ይበዛል።እነዚህ ምሳሌዎች ብቻ ሳይሆን ሌላም አለ፡፡መዝሙሩ።በልደት በዓል በመላእክት የተዘመረው መዝሙር በጣም አጭር መዝሙር።ነገር ግን የክርስትናችን መጠሪያ ሆነ።"ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ"(ሉቃስ 2:14)ጥቂት ቃላት ግን ትልቅ ተጽእኖ ያለው መዝሙር።የክርስትናችን ገላጭ መጠሪያ ሆነ።ለምን?ምክንያቱም ይህ መዝሙር ሰማይን፣ ምድርን እና የሰውን ዘር የያዘ ነው።ስለዚህም ሁሉን አቀፍ መዝሙር ሆነ።ሰማይ፤ ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን።ምድር፤ ሰላምም በምድር። የሰው ዘር፤ ለሰውም በጎ ፈቃድ።የተሟላ እና ሁሉን የሚያጠቃልል መዝሙር ሆነ።ለክርስቶስ ሥራ እና ለክርስትና ተልእኮ መጠሪያ ሆነ።ይህም ለሰው ልጅ ህይወት እንደ እቅድ እና ፕሮግራም ነው።ስፍር ቁጥር የሌላቸው ምሳሌዎች አሉ።ሆኖም ፣ ዋናው ነገር ይህ ነው፤ትንሹን ነገር በእግዚአብሔር እጅ ስታስቀምጠው ታላቅ ይሆናል።በቋንቋችን፡ "የተባረከ ነው" እንላለን፤ ምንም እንኳን ትንሽ ቢሆንም።

ከልደት ታሪክ ባሻገር፣ ሌሎች ምሳሌዎችን ልሰጣችሁ እችላለሁ።ለምሳሌ አምስት እንጀራና ሁለት ዓሣ የያዘው ትንሽ ልጅ። በሺዎች በሚቆጠሩ ሰዎች መካከል።ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ሕዝቡን እንዲመግቡ ባዘዛቸው ጊዜ፣«ከትንሽ ብላቴና በቀር ሌላ ነገር የለንም» አሉ።«ከአምስት እንጀራና ከሁለት ዓሣ ጋር » (ዮሐንስ 6፡9)ምናልባትም ይህ የልጁ ምግብ ነበር። ነገር ግን ደቀ መዛሙርቱ ይህን በጣም ትንሽ ምግብ ወሰዱ፣ በክርስቶስ እጅ አስቀመጡት እና ተባዛ።ሴቶችንና ሕፃናትን ሳይጨምር አምስት ሺህ ወንዶችን መገበ።የተረፈውም አሥራ ሁለት መሶብ ነበረ።እንዴት ያለ መትረፍረፍ ነው! እንዴት ያለ ታላቅ በረከት ነው!

ሌላ ምሳሌ እንመልከት፤ ሐዋርያዉ ጴጥሮስ ከሐዋርያነቱ በፊት ዓሣ አጥማጅ ነበር።ዓሣ አጥማጅ ነበር። ዓሣ ለማጥመድ ወጣ። እና ዓሣ አጥማጆች እንደሚሉት፣ “የእሱ መተዳደሪያ በእግዚአብሔር ላይ የተመሰረተ ነው።”አንድ ቀን አቅርቦት አለ፣ ሌላ ቀን የለም።ያልተሳካ የዓሳ ማጥመድ ሌሊት ነበር።ዓሳ ለማጥመድ ሌሊቱን ሙሉ ሲደክሙ ቆይተዋል፤ ግን አልተሳካላቸውም። ክርስቶስ ጎህ ሲቀድ ተገለጠና እንዲህ አላቸው።"መረቦቻችሁን ጣሉ" (ሉቃስ 5:4)። ጴጥሮስ ታዋቂ ቃሉን ተናገረ፣“ሌሊቱን ሁሉ ስንደክም አድረን ምንም አልያዝንም፣ነገር ግን በቃልህ መረቦቹን እጥላለሁ” (ሉቃስ 5፣5)።መጽሐፉ እንዲህ ይላል፣ “…ይህንም ባደረጉ ጊዜ እጅግ ብዙ ዓሣ ያዙ፤ መረቦቻቸውም ተቀደዱ” (ሉቃስ 5፡6)።በክርስቶስ ቃል መረቦቹ ተቀደዱ፣ ሞሉ እና ጎረፉ።"በቃልህ መረቡን እጥላለሁ" (ሉቃስ 5፣ 5)

ሌላ ቆንጆ ምሳሌ አለ፤ሁለት ሳንቲም የሰጠችው ሴት (ማርቆስ 12፡42)።እነዚህ ሁለቱ ሳንቲሞች በጌታ ክርስቶስ ጊዜ ዋጋቸው በጣም ትንሽ ነበር።ነገር ግን ከድህነቷና ከፍላጎቷ ሰጥታቸዋለች።በውጤቱም እግዚአብሔር አመሰገናት እና ከሰው ለይቶ ወደ እሷ አመለከተ።ሁለት ሳንቲም የሰጠችዉ ሴትም በአዲስ ኪዳን ታዋቂ ሆነች።ብዙ የሰጡ ሌሎች ሲኖሩ።እናም በዚያን ጊዜ የነበሩት ሳንቲሞች ብረት ነበሩ።የሚሠጥበት ሣጥንም ብረት ነበር።ሳንቲሞች በሳጥኑ ውስጥ ሲቀመጡ፣ ድምጽ ያሰሙ ነበር። ትላልቅ ሳንቲሞች ከፍተኛ ድምጽ ያሰሙ ነበር።ትናንሽ ሳንቲሞች ያነሰ ድምጽ ያሰሙ ነበር።እነዚህ ሁለት ሳንቲሞች ምናልባትም ምንም ድምፅ አልሰጡም።ክርስቶስ ግን አመስግኗታል፡ ባርኳታል፡ ጠቆማትም።አርአያ ሆነችን።

የክርስቶስን አገልጋዮች በመምረጥ ታሪኮች ውስጥ እንኳን እንደ ነቢዩ ዳዊት ምርጫ (1ሳሙ 16፡11)።እሱ ወጣት ልጅ ነበር፣ ከወንድሞቹ መካከል ትንሹ፣ በተፈጥሮም ደካማ።በቅዱስ ቢሾይም ተመሳሳይ ታሪክ ይታያል።ዳዊት ወጣት ነበር፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ባሪያ አድርጎ በመረጠው ጊዜ ሽማግሌዎቹ፣ “ትልቅ ሰው ምረጥ” ብለው ተቃወሙ።እግዚአብሔር ግን ወጣቱን መርጦ ታላቅና ቅዱስ ሰው አደረገው።ዳዊትን ባለ ሙሉ ሕይወቱና መዝሙሩ ነቢይ አደረገው።የታወቀው የንስሐ መዝሙርን ጨምሮ።

ይህ ውብ ምሳሌ የክርስቶስን ልደት ስናከብር የሚያስታውሰን ነገር አለ።ለእግዚአብሔር የምናቀርበው ትንሽ ነገር ሁሉ እጅግ ታላቅ እንደሚሆን ያስታዉሰናል።የገንዘብ ትንሽ ብቻ ሳይሆን የጊዜ ትንሽም ጭምር ነው።ከቀናችሁ ውስጥ በጣም የተወሰነ ጊዜ ለእግዚአብሔር ስትሰጡ፣ በጸሎት፣ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ፣ በብቸኝነት ወይም በማሰላሰል፣ለእግዚአብሔር ያቀረባችሁትን እነዚህን ጥቂት ጊዜያት፣መላ ቀናችሁን፣ ሳምንታችሁንና ወራችሁን ባርከዉት ታገኛላችሁ።ጥረትን፣ አገልግሎትን፣ ሀሳቦችን ወይም ፈጠራን ስታቀርቡ፣ የቱንም ያህል ትንሽ ብትሰጡ ታላቅ ይሆናል።ወዳጆች ሆይ ዛሬ የማቀርብላችሁ የክርስቶስ ልደት መልእክት ይህ ነው።መጠኑ እና ቅርጹ ምንም ይሁን ምን ማንኛውንም ነገር አቅልላችሁ አትመልከቱ።ትናንሽ ልጆቻችን ወደፊት ታላቅ ይሆናሉ።የምታቀርቡት ጥረት፣ ጊዜያችሁ፣ ገንዘባችሁ፣ ሀሳባችሁ፣ ጉልበታችሁ እና እንባችሁ፣ ስለ እርሱ ከቀረበ ሁሉም በእግዚአብሔር እጅ ታላቅ ይሆናል።

ሁላችሁንም እንኳን አደረሳችሁ።በአለም ዙሪያ ላሉ የኮፕቲክ አህጉረ ስብከት በሙሉ እንኳን አደረሳችሁ እላለሁ።በአፍሪካ ፣ በእስያ ፣ በአውሮፓ፣ ሰሜን አሜሪካ፣ ደቡብ አሜሪካ እና አውስትራሊያ፣ደግሞም በታላቁ የአምላካችን ከተማ ኢየሩሳሌም የቅድስት ሀገር መንበር።ከካይሮ፣ ከግብፅ ሁላችሁንም እንኳን አደረሳችሁ እላለሁ።እንኳን አደረሳችሁ እያልኩ የመላው የግብፅ ኮፕቲክ ቤተክርስቲያን ሰላምታ አስተላልፋለሁ።መልካም አዲስ አመት እመኝላችኋለሁ። የተባረከ የልደት በአልና በህይወታችሁ የክርስቶስ ልደት ደስታን እመኝላቸዋለሁ።"ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ" (ሉቃስ 2:14).

Tawadros II